በቀለዱብን ላይ....

ዮናስ 03-03-16

በአሁኑ ጊዜ በአገራቱ ውስጥ በጉልህ ከሚታዩ ችግሮች መካከል የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ የፍትሕ መጓደልና ሙስና ተጠቃሽ ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ በአገራቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመከሰት ላይ ያሉ ብጥብጦች፣ የዜጎች ሕይወት ሕልፈት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት በጣም ያሳስባሉ። በተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ የሚታዩ ብልሹ አሠራሮችና ሕገወጥነቶች መብዛት የምሬት ምክንያት ናቸው።

እንዲህ ዓይነት ተደራራቢ ችግሮች ያሉባት አገር ተደላድላ መቀመጥ ስለማይቻላት፣ መንግሥትን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ መላ ሊመቱ ይገባል። የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ በመካከለኛ ደረጃ ያሉ አመራሮችና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት እርስ በርስ እየተፈራሩ የሚሸፋፍኑ ከሆነ አገሪቱን የማትወጣበት አዘቅት ውስጥ ነው የሚከቷት። የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችም እነዚህን ችግሮች ከማጋለጥ ጀምሮ የመፍትሔ ሐሳብ በማመንጨት የአገር ባለቤትነት ስሜት ማሳየት አለባቸው። መንግሥትን የሚመሩ አካላትም ዜጎች በነፃነት ተሳታፊ እንዲሆኑና የመፍትሔ አካል መሆናቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል። የሕግ የበላይነት ልዕልና እንዲያገኝና ሕገወጥ ተግባራት እንዲወገዱ ሲፈለግ፣ የዜጎች መብትና የተሳትፎ ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የአገራቱ ዜጎች በማያስማሙዋቸው ዋነኛ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም እየያዙና ልዩነቶቻቸውን ደግሞ በሠለጠነ መንገድ እያንፀባረቁ ችግሮችን ለመፍታት መትጋት አለባቸው። በዚህች አገር ውስጥ በጣም መለመድ ያለበት ዓቢይ ቁም ነገር ማንም ሰው ባለሥልጣንም ይሁን ምን ከሕግ በታች እንደሆነ መረጋገጥ አለበት። ሕግ ባለበት አገር ውስጥ ራሳቸውን ከሕግ በላይ የሚያደርጉ ወይም የአምባገነንነት ባህርይ ያላቸው ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም። በመሆኑም ዜጎች ራሳቸውን ከሕገወጥ ተግባራት እያራቁ ለሕግ የበላይነት መስፈን መትጋት አለባቸው። ችግሮች የፈለገውን ያህል ውስብስብ ቢመስሉም በተባበረ ክንድ ስለሚፈቱ፣ በተቻለ መጠን የያገባኛልና የባለቤትነት መንፈስን ማጠናከር ተገቢ ነው።

ብዙ ጊዜ በመንግሥት በኩል የሚስተዋሉ ችግሮች ባለቤት የሌላቸው ይመስል ችላ ሲባሉ ይታያል፡፡ ነገር ግን በየደረጃው ኃላፊነት የተሰጠው ተቿሚ መፍትሔ አመንጪ መሆን ሲገባው ወደሌላ ማላከክን ስራው ሲያደርገው ማየት የተለመደ ነው፡፡ ወደ መንግሥት ተቋማት አገልግሎት ፍለጋ የሚሄዱ ዜጎች ጉዳያቸውን በአቋራጭ ለማስጨረስ ከሚሯሯጡ ይልቅ፣ በቀጥተኛው መንገድ መብታቸውን ማስከበር ከዚህ በሁዋላ መልመድ ግድ የሚላቸው ይሆናል ፡፡ ብልሹ አሠራሮች የሚንሠራፉት እያንዳንዱ ዜጋ መብቱን በሕጋዊ መንገድ ማስከበር ሲያቅተው ነው፡፡ ፍትሕ ፍለጋ ፍርድ ቤቶች የሚሄድ ዜጋ ፍትሕ ሲነፈግ ማጋለጥ አለበት፡፡ በመማለጃ ወይም በጉቦ ፍትሕ ለማግኘት ከመሞከር ይልቅ፣ መብትን በሕጋዊ መንገድ ማስከበር በራሱ አንዱ የመልካም አስተዳደር አካል መሆን ነው፡፡ ራስ ወዳዶች የአገር ሀብት ሲዘርፉ በይሉኝታ ከማየት ይልቅ፣ በአደባባይ አጋልጦ ክብር ማግኘት ያስደስታል፡፡ ምንም እንኳ መስዋዕትነት የሚያስከፍል ቢሆንም፣ ለአገር ህልውና ሲባል ራስን መስጠት ግን የግድ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ዘርፍ የሚታየውን ሥር የሰደደ ችግር ለመፍታት በተወሰደው ዕርምጃ፣ ተጠያቂ ይሆናሉ በተባሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ላይ ክስ ለመመሥረት ሚያስችል መረጃዎች ከህብረተሰቡ መሰብሰቡም አንዱና ዋነኛው የአሳታፊነትና የተሳትፎ መገለጫ ነው ፡፡ በአመራሮችና በሠራተኞች ላይ የተጠናቀረው መረጃ ለሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን መላኩን የተመለከቱ ዘገባዎች መስማታችንም ስለዚሁ እና ስለንቅናቄው የሚያበረታን ነው ፡፡በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠያቂ ይሆናሉ የተባሉ ሠራተኞች በቁጥጥር ሥር እየዋሉ መሆኑም ተሳትፍ የተባለውን ህዝብ የሚያነቃ ነው ፡፡

በመሬት መዋቅር ሠራተኞች ላይ የሽግሽግ፣ የምደባና የማጥራት ሥራዎችን ለማከናወን በተካሄደው ጥናት በርካታ ሰዎች ተጠያቂ እንደሚሆኑ መረጋገጡ ግን አስደንጋጭ ነው ፡፡ምክንያቱ ደግሞ የት እንዳለን ማመላከቱ ነው፡፡

እነዚህን አመራሮችና ባለሙያዎች ተጠያቂ ማድረግ ያስችላል የተባሉ ተጨማሪ ማስረጃዎች እየተለቀሙና እየተጠናቀሩ ለፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን

እየተላኩ መሆኑ ተመልክቷል። በተጨማሪም በተጨባጭ ተሳትፎ ያላቸው እንደሆኑ ተገልጿልና።

የአዲስ አበባ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ምንጮች እንደገለጹት፣ ተጠያቂ ከሚሆኑ ሠራተኞች በተጨማሪ ከነጭራሹ የሚሰናበቱ ሠራተኞችም አሉ። የተቀሩት ደግሞ በሌሎች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች እንዲመደቡ ዝርዝራቸው ለሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ተልኳል።

በተለያዩ መድረኮች የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ከማዕከል ጀምሮ እስከ ክፍላተ ከተሞች ድረስ ያሉ የመሬት መዋቅሮች የፈጠጠ ሙስና የሚታይባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ያለ እጅ መንሻ ጉዳይ ማስፈጸም የማይቻል መሆኑን ማህበረሰቡ መቼም ሳይዘነጋ በምንጣሮው ስራ ንቁ ተሳታፊ መሆን ይጠበቅበታል።

ከዚህ በተጨማሪ ደላሎች የራሳቸውን ኔትወርክ ከሠራተኞች ጋር በመመሳጠር የዘረጉ በመሆናቸው፣ እጅግ አስቸጋሪ ቡድን እየተፈጠረ መሆኑ ነዋሪዎች በግል የገጠማቸውን በማንሳት አቤቱታ ሲያቀርቡ መቆታቸውንም ስለንቅናቄው ለአፍታ መዘንጋት የለባቸውም።

በሁሉም ክልሎችና በአዲስ አበባ በተደረገው ጥናት ከመሬት ልማት ዘርፍ ጋር ተያይዞ ከተነሱ ዋና ዋና ችግሮች መካከል የኪራይ ሰባሳቢነት አንዱ መሆኑ የማይዘነጋና የሁል ጊዜም አጀንዳ ነው። ይህም ሙስና አለ፣ ጉቦ መስጠትና መቀበል አለ፣ ከጉቦ ውጪ የሚሰራ ስራ የለም እንዲያውም ጉቦ መብላት ስራ ሆኗል በሚል የተደጋገመ የህዝብ ሮሮ የሚገለጽ ነው። በእያንዳንዱ የሊዝ ጨረታ አስቀድሞ ለጨረታ የሚወጡ ቁራሽ መሬቶች በችካል ተለይተው ወደ ጨረታ አይቀርቡም፤ ለድርድር በሚመች መንገድ በጅምላ ለጨረታ ይቀርቡና ገንዘብ ለሚሰጡ የተመቹና የሚመርጧቸው ቦዎታች መስጠት የተለመደና ህጋዊ ሚመስል የነበረ መሆኑ አይዘነጋምና የእርምጃው ተገቢነት ዘገየ ካላስባለ በስተቀር ተገቢነቱ አያጠያይቅም፣ በሁሉም ከተሞች እንደሚባለው በመጀመሪያ ለባለሙያውና ለአመራሩ በቤተሰብ፣ በአገር ልጅነትና በጓደኝነት አግባብ ያልሆነ ትስስር

ለመፍጠር ይሰራል፣ ያለ ገንዘብ /ጉቦ/ የሚፈፀም ነገር የለም ብሎ የመደምደምና፣ በባለሃብቶቹ በኩል ደግሞ አለማልማትና መሬት አጥሮ ማስቀመጥ አንዲሁም በስታንዳርዶች በትክክል ስለማይሰሩ በጉቦ እንዲፈጸምላቸው ወይም እንዳይጠየቁ ሲሉ ጉቦ የመስጠት ሁኔታ እንደሚታይ እና ይህ ዝንባሌ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ መምጣቱ ነው፡፡

ወደ አመራር የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከመወሰን ይልቅ መልሶ ለባለሙያው መመለስ ወይም ኮሚቴ አቋቁሞ ለኮሚቴ መምራት የተለመደ ተግባር ነው፡፡ በመሬት ላይ በየጊዜው አመራር ቢቀያያርም አሁንም የሚመጣው አመራር የስራዎች ምልልስና ደብዳቤ መመራራት አለማስቀረቱ የተለመደና ሌላው ህጋዊ የመሰለው አሰራር ነው፡፡ ከዚህ ሌላ አመራሩ በርካታ ጊዜውን ስብሰባ ላይ ስለሚያሳልፍ የተገልጋዮች ምልልስ አለ፡፡ አብዛኛው አመራር ለብዙ ጊዜ በስብሰባ ሰበብ በቢሮ ውስጥ አይገኝም፡፡ አመራሩና ሰራተኞች በተለያዩ ምክንያቶች ለረዥም ጊዜ ቢሮ በመዝጋት ባለጉዳዮች እንደሚመላለሱና እንደሚንገላቱም ይታወቃል ፡፡

በአዲስ አበባ በመሬት ዘርፍ ያለው አመራር በዘርፉ ለሚታዩ ችግሮች እና ከተገልጋዩ ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎችን መርምሮ ወቅታዊ ውሳኔና ምላሽ ከመስጠት አንጻር ችግሩ የሰፋ የነበረ መሆኑ ይታወቃልና እርምጃው ተገቢ ነው፡፡ ውሳኔ ላለመስጠት ደግሞ ስብሰባና ስልጠና የአመራሩ መደበቂያ ምሽግ የነበረ መሆኑም ይታወቃል፡፡ አልፎ አልፎም ሰብሰባ ነኝ በሚል ቢሮ ዘግቶ ወጥቶ በዚያው መጥፋት፣ ባለጉዳይን በቀጠሮ መሠረት አለማስተናገድ፣ለሚቀርብ ቅሬታ ፈጣን ምላሽ አለመስጠት፡፡ ለምሳሌ ውክልና ሳይሰጥ ለ3 ወራት ያህል ስልጠና ሄዶ የመጣ አመራር በኛ ሰፈር አለ፡፡ ሌላው በማኔጅመንት ኮሚቴ የሚታዩ ጉዳዮችን ቶሎ አለማየትና ውሳኔ አለመስጠት፣ ለሌላ ጊዜ እየተባለ ቀጠሮን ማብዛት በአመራር ዘንድ የሚታይ ሰፊ ችግር የነበረ መሆኑም ይታወቃል፡፡

የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ድርጊት መስፋፋት በሰራተኛውም ሆነ በሌላው ዜጋ ሰርቶ መለወጥን ሳይሆን አለአግባብ መሬት በመውሰድ በአቋራጭ የሚከብሩበትን መንገድ ብቻ የመፈለግ አመለካከት እንዲጨምር አድርገዋል፡፡ ይህ አመለካከት ደግሞ ልማታዊ እና ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን በመሸርሸር የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ የበላይነት እንዲኖረው በማድረግ የተወሰኑ ጥቂት ግለሰቦች ብቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ፍትሃዊነትና እኩል

ተጠቃሚነት እንዳይኖር በማድረግ የተጀመረውን ፈጣን ልማት የሚያደናቅፉ ሲሆን ህብረተሰቡም በመንግስት ላይ እምነት እንዲያጣና ስርዓት አልበኝነት እንዲሰፍን በማድረግ በአጠቃላይ ስርዓቱን አደጋ ላይ ይጥለዋል፡፡ በተለይ ደግሞ የመሬት ስርዓቱ ልማታዊ ባለሃብቱን ከማበረታታት ይልቅ በልማቱ ላይ ምንም እሴት የማይጨምሩ የመሬት ደላሎችና ኪራይ ሰብሳቢ ባለሃብቶችና ባለስልጣኖች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የተዛባ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር በማድረግ ህብረተሰቡ በመንግስት ላይ እንዲነሳ የሚያደርግ ይሆናልና ጉዳዩ በዘመቻ ብቻ ሳያበቃ በተጠናከረ መልኩ ሊቀጥል ይገባል፡፡